# በቶሮንቶ የተካሄደውን የፍኖተ ዴሞክራሲ ሬዲዮ ምሽት የትውልዱ ትውስታ ፊልም አጀበው፤

በቶሮንቶና አካባቢው የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ በSEPTEMBER 19, 2009 ዓ/ም ያዘጋጀው የርዳታ ማሰባሰብና የትግል አንድነት ምሽት በተሳካ ሁኔታ ተፈፅሚል። ፍኖተ ዴሞክራሲ ሬዲዮ በሀገራችን ኢትዮጵያ ላለፉት ረጅም አመታት በተካሄደውና እየተካሄደ ባለው ኢትዮጵያን ነፃ የማውጣት ትግል ውስጥ በወያኔ ፀረ ነፃ ፕሬስ እርምጃ የተከሰተውን የዜናና መረጃ ክፍተት ከመሸፈን ባሻገር ወያኔና ቡችሎቹ እንኳን ሊክዱት በማያስችል ሁኔታ የትግሉ መረጃ ምንጭና አቀጣጣይ ነዳጅ በመሆን ከአንድ ህዝባዊ መገናኛ ብዙሃን የሚጠበቅ ታላቅ የአርበኝነት ገድል አስመዝግቧል። የህዝብ ወገናዊነቱንም አስመስክሯል። ፍኖት በወያኔ ጓዳ ከሚተበተበው ህቡዕ ሴራ አንስቶ በግልፅ አደባባይ እስከሚከናወነው ፍልሚያ ያለውን እውነታ ለህዝባችን ከማሳወቅ ባሻገር ፖለቲካዊ ክህሎትን የተላበሰ የትግል አቅጣጫ ጠቋሚና አመላካች የመሆን አቅም ያለው ዘገባ በማቅረብ ታላቅ አስተዋፅዖ አበርክቶዋል። ይህንንም ቅዱስ ተልዕኮ የህዝቧና የግዛት አንድነቷን የሚያስከብር ሁሉን አሳታፊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በሀገራችን ምድር እውን እስኪሆን ይቀጥላል። ፍኖት የትግሉ ደረጃ ብስለትና ፅናት መገለጫም መሆኑን በማያጠያይቅ ሁኔታ አረጋግጧል።

ፍኖት ይህን ሁሉ ይበል የሚያሰኝ ተግባር ሲያከናውን ጉዞው ሁሉ አልጋ ባልጋ ሳይሆን ከቀጥታና ስውር ወያኔዎች እንዲሁም ከውስጡ በበቀሉ ተቀናቃኞች የውስጥና የውጭ እሳት እየተለበለበም ነበር። ባንድ ወቅት ፍኖትን ከተቻለ ለሰላሳ ተቃዋሚ ለማድረግ ካልተቻለ ደግሞ ድራሹን ለማጥፋት የተነሱ ትግል አዘናጊ አልባሌዎች የፕሮግራሙን ይዘትና የአዳማጩን ብዛት በማጣጣል የሀሰት ዘመቻ ከፍተውበት እንደነበር የሚታወስ ሲሆን ይህ ተራ ማደናገር ግን ባዶነቱና አደገኛነቱ በጊዜ ውስጥ ተረጋግጧል።

በዕለቱ የተካሄደውን ዝግጅት ተጨማሪ ሞገስ ያላበሰው ደግሞ በዕውቁ ገጣሚና የመብት ታጋይ አሊ ሁሴን ተዘጋጅቶ በአውሮፓና በአሜሪካ የተለያዩ ከተሞች ተመልካቾች ዘንድ ከፍተኛ አድናቆት ያተረፈውን ”የትውልዱ ትውስታ” “MEMOIRS OF THE GENERATION” የተሰኘው በደራሲው የግል ህይወትና የትግል ተሞክሮ ላይ የተመሰረተው ታሪካዊ ፊልም ነው። ይህ 1ሰዓት ከሰላሳ ደቂቃ ያህል የሚፈጅው ዶኪመንተሪ ፊልም አያሌ ቁም ነገሮችን ያዘለ ሲሆን በዋናነት ግን ያ-ትውልድ ለምን የአፄውንና የደርግን ሥርአቶች እንደታገለና አሁን ደግሞ ፀረ ኢትዮጵያ የሆነውን ቡድን እየተፋለመ እንደሚገኝ የትውልዱን ታሪክ ሊወክል የሚችለውን የዓሊ ሰዒድን ታሪክ በዋቢነት ያቀርባል። ጭቆናና የመብት ረገጣ ባለበት ሁሉ ትግል የተፈጥሮ ህግን ያህል አይቀሬ መሆኑንም ገሀድ ያደርጋል ፊልሙ። የደርጉም ዘመን ኢሰብአዊ ግፍ በሰለባዎቹ አንደበት ይተረካል። ዘግናኝ ቢሆንም የታሪካችን አሳፋሪና አሳዛኝ ቅርስም ሆኖ ይኖራል። እውነቱን እንዳለ የማቅረቡም ምክንያት ታሪኩ ይህን ሀቅ ቢዘል ሸራፋ ታሪክ መሆኑ ብቻ ሳይሆን መጪውን ትውልድም ከታሪካችን ሊማር የሚገባውን ዋነኛ ጉዳይ ማሳጣትም እንዳይሆን ነው። ሰለባዎቹ ሊሸከሙት የተገደዱት ግፍና አበሳም የነፃነት ዋጋው እስከምን ሊደርስ እንደሚችል ትግሉን የተቀላቀሉ በተለይም በመሪነት ሚና ላይ ያሉ ሁሉ ቆም ብለው ህሊናና ፅናታቸውን ዳግም እንዲፈትሹም ያሳስባል።

አቶ ዓሊ በፊልሙ መጨረሻ እንዳስገነዘቡትም ታሪኩ አደባባይ ወጥቶ መነገሩ ቂምን ለመቀስቀስና በቀልን ለማውረስ ሳይሆን ሁኔታው ዳግም እንዳይፈፀም ለማሳሰብም ጭምር ነው። ደርግ “የቀይ ሽብር አብዮታዊ ኮሚቴ’ በሚል ይፋ መዋቅር አማካይነት ያካሄደው አገር አቀፍ ሽብር በዘመነ ወያኔ ህቡዕ ገብቶ ከቀደሙቱ እነ ፀጋዬ ደብተራው፣አበራሽ በርታ፣ አበራ የማነ አብ እንዲሁም ብርቱካን ሚደቅሳ ሺብሬ ደሳለኝና ሌሎች በአስር ሺዎች ለሚቆጠሩ ትኩስ ሰለባዎች ነፃነት መሙዋገት ግዴታ እንደሆነ ያሳስባል።

በፊልሙ መጨረሻ (የ 84 አመት ዕድሜ ባለፀጋ የሆኑት የደራሲው ወላጅ እናት) የወያኔን ሥርአት ነፍሰ ገዳይነትና አገር አጥፊነት ካወሱ በኋላ ሥርአቱ በመረረ ትግል እንጂ በምልጃ እንደማይወገድ ይህ እንዲሆን መመኘትም ታላቅ ስህተተ እንደሆነ ልጃቸውን (ዓሊን) “ከመሞቴ በፊት አንተን ማየትን ያህል የምመኘው ነገር የለም ይሁን እንጂ ይህ ዘረኛ ቡድን እያለ መጥተህ ታሪክህን እንዳታበላሽ” በማለት ሲያስጠነቅቁት በዕድሜ ልጆችና የልጅ ልጆቻቸው ለሚሆኑ ሁሉ ጥልቅ ማሳሰቢያ ነው።

በምሽቱ ዝግጅት ጥሪውን አክብረው በሥፍራው የተገኙ ወገን የሆኑ የአንድነት ሀይላት ለዝግጅቱ መሳካት ያሳዩት ልባዊ ትብብር የብዙዎቻችንን ልብ ያሞቀ የወገናዊነት መገለጫ ነበር ትንሿ የትብብር መንፈስ ታላቅ የአለኝታነትን ስሜት የመፍጠር ሀይል እንዳላትም አስረጂ ነበር።

የቶሮንቶና አካባቢው የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ደጋፊ ኮሚቴ ጥሪያችንን አክብረው የመጡትን ከሁሉም በላይ ደግሞ ለዝግጅቱ መሳካት የተባበሩ ወገኖቸን ከልብ ያመሰግናል።

የነፃነቱ ትግል ይቀጥላል!

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!

ነፃ ፐሬስ የህዝብ አይንና ጆሮ ነው!